የኢፌድሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ቴክኖቢዚያ የኢንዱስትሪ ውጤቶች ልማት ኢንተርኘራይዝ

# የተሽከርካሪ ጥገና (ጋራዥ) እና እድሳት አገልግሎት የውል ስምምነት

1. የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲቲዩት(ከዚህ ቀጥሎ ኢንስቲትዩቱ ተብሎ ይጠቀሳል)

የውል ሰጪ አድራሻ

- የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲቲዩት
- በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05
- የስልክ ቁጥር 0116612244
- ፖስታ ሳጥን ቁጥር 30726

ውል ተቀባይ ፡- የኢፌድሪ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ቴክኖቢዚያ የኢንዱስትሪ ውጤቶች ልማት ኢንተርኘራይ

አድራሻ ፡- ክ/ከተማ ወረዳ የቤት ቁጥር

ስልክ 0912901236/0911428217

ከዚህ በላይ ውል ሰጪ እና ውል ተቀባይ ተብለው በተጠቀሱት መካከል ከዚህ ቀጥሎ "የተሽከርካሪዎች ጥገና እና ዕድሳት ውል" በመባል የሚታወቅ የውል ስምምነት ዛሬ 01/11/2018 ቀን 2018 ዓ.ም. ተፈርሟል፡፡

## አንቀጽ 1

## የውሉ ዓላማ

ውል ሰጪ የሚገለገልባቸውን መኪናዎች በጋራዥ አስጠግኖ አሳድሶ የተቀላጠፈ አገልግሎት ማግኘት ሲሆን ውል ተቀባይም የውል ሰጪ መኪናዎች ጠግኖና አድሶ የሠራበትን ሥራ ማግኘት ነው፡፡

## አንቀጽ 2

## የውሉ አካል የሆኑ ሰነዶች

ውል ተቀባይ በጨረታው አሸናፊ የሆነበት የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ወይም የመንግስት ኤሌክትሮኒክስ ግዥ ስርዓት (Egp) ላይ የተቀመጡ ሰደዶች የዚህ ውል ስምምነት አካል ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 3

## የውል ስምምነቱ መሠረቶች

3.1 ውል ሰጪ ለሥራ የሚገለገልባቸው መኪናዎች ሲበላሹ ውል ተቀባይ ማደስ መጠገን አጥቦ ዘይትና ቅባቶችን መለወጥና ሌሎች አገልግሎቶች ከማድረጉ በፊት የብልሽቶችንና ጉዳቶችን ዓይነትና ደረጃ መርምሮና አይቶ የሚያስፈልገውን የጥገና እና የዕድሳት የአገልግሎት ዓይነትና

ዋጋውን ለውል ሰጪ ከገለፀ በኋላ ውል ተቀባይ ሥራው ይቀጥል ብሎ ሲያሳውቀው ተሽከርካሪውንና ደባል ንብረቶችን በርክክብ ቅጽ ተረክቦ የተጠየቀውን ዕደሳ ጥገና እና የእጥበት አገልግሎቶችን በመስጠት ተሽከርካሪውን ውል ተቀባይ በሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሠርቶ በማስረከብ ሂሳቡን በውለታው መሠረት እንዲከፈለው ይጠይቃል፡፡

3.2 ውል ተቀባይ ከዚህ ውል ጋር ተያይዞ በሚገኘው የእጅ ዋጋ መጠየቂያ ቅጽ በሰጠው ዋጋ መሠረት የመኪና ብልሽቶችን መጠገን የዕደሳ ሥራዎችን የመሥራት መኪና አጥቦ ዘይትና ቅባቶችን ለመለወጥና የመሳሰሉትን በድርጅቱ ሊስተናገዱ የሚችሉ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ የክፍያ መጠናቸውም በዋጋ ማቅረቢያ ፕሮፎርማ ቅጽ ላይ በቅድሚያ ሊገለፁ የማይችሉትን የሥራ ዓይነቶች በተመለከተ ውል ተቀባይ እና ውል ሰጪ የሚወሰን ይሆናል፡፡

3.3 ውል ተቀባይ በአንቀጽ 3.1 እና 3.2 የተዘረዘሩትን አገልግሎቶችና ጥያቄዎች የሚያስተናግደው የሚመለከተው ኃላፊ ፊርማና የውል ሰጪ ክብ ማኅተም ያረፈበት መጠየቂያ መቅረቡ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

3.4 ውል ሰጪ ለጥገና ያቀረበው መኪና በትዕዛዙ መሠረት መጠገኑና በአግባቡ በአስተማማኝ ብቃት መሠራታቸውን በባለሙያ አረጋግጦ ከውል ተቀባይ ይረከባል፡፡

3.5 ውል ተቀባይ ካረጋገጠው እና ከተስማማበት ብልሽት ሌላ የጥገና ሥራ የሚያስፈልገው ተጨማሪ ብልሽት ካጋጠመ ውል ተቀባይ ተጨማሪ ብልሽት መገኘቱን ለውል ሰጪ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ውል ሰጪ ብልሽቱን አይቶና አረጋግጦ ተጨማሪ ጥገና እንዲደረግ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

## <u>አንቀጽ 4</u>

## <u>የውል ሰጪ መብትና ግዴታ</u>

4.1 ተሽከርካሪዎቹ በሥራ ትዕዛዙ መሠረት ተገቢው ጥገናና ዕድሳት የተደረገላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ የሚጠየቁ ክፍያዎች የክፍያ ጥያቄው እንደቀረበ ሂሳቡን የመክፈል ግዴታ አለበት

4.2 ጥገና እና ዕደሳ የተደረገላቸው መኪናዎች ውል ሰጪ አይቶና ፈትሾ የመረከብ ጉድለቶች ቢኖሩ ከመውጣቱ በፊት እንዲስተካከሉ የማዘዝ መብት አለው፡፡

## <u>አንቀጽ 5</u>

## <u>የውል ተቀባይ መብትና ግዴታ</u>

5.1 ውል ተቀባይ ሊጠግንና ዕደሳ ሊያደርግላቸው ዘይትና ቅባት ለመቀየር በተረከባቸው

ተሽከርካሪ መኪናዎች ላይ_በጋራዥና ከጋራዡ ውጭ_ለፍተሻ ሲንቀሳቀሱና ወይም ቆመው ለሚከሰቱ አደጋዎች ማለትም ተሽከረካሪዎች ቢሰረቁ ቢጋጩ ደባልና ተጓዳኝ ዕቃዎች ቢጎድሉ ቢጠፉ ወይም በእሳት የመቃጠል አደጋ ቢፈጠር በፍተሻ ላይ ሲያሽከረክሩ አደጋ ቢያደርሱና ቢደርስባቸው ሌሎችም ያልተጠቀሱ አደጋዎች በተሽከርካሪ መኪናዎችና ደባል ዕቃዎች ላይ ቢደርሱ ሙሉ በሙሉ ውል ተቀባይ የንብረቶቹ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

5.2 በአዲስ የተተኩ አሮጌ መለዋወጫዎችን አዲስ መለዋወጫ እንደተገጠመ ማሳየት ውል ተቀባይ አሮጌውን ዕቃ ለውል ሰጪ ተወካይ ማስረከብ ግዴታው ይሆናል፡፡

5.3 ውል ተቀባይ ለጠገናቸውና ዕደሳ ላደረገላቸው ተሽከርካሪ መኪናዎች ከዚህ በታች የተገለጸውን በዋስትና ጊዜ ውስጥ የሚበላሹትን በራሱ ወጪ ይጠግናል፡፡

ኸውም፡-

ሀ/ ለሞተር ሙሉ ዕድሳት ለተደረገላቸው 3 (ሶዎስት ወር) ወይም 5000 ኪሎሜትር ዋስትና ይሰጣል፡፡ ነገር ግን ሞተር ሙሉ ዕድሳት ተደርጎለት በውል ሰጪ የአጠቃቀም ስህተት ለሚፈጠረውም ሆነ ለሚከሰተው ብልሽት ውል ተቀባይ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፡፡

ለ/ ለካምቢዩ ዲፈረንሻል ሙሉ ዕድሳት ለሚደረግላቸው 3 (ሶዎስት ወር) ይሰጣል፡፡ በተመሳሳይ ለካምቢዩና ዲፈረንሻል ሙሉ ዕድሳት ተደርጎለት በውል ሰጪ አጠቃቀም ስህተት ለሚፈጠረውም ሆነ ለሚከሰተው ብልሽት ውል ተቀባይ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፡፡

ሐ/ ከኤሌክትሪክ ክፍሎችና የፍሬን ሸራዎች እንዲሁም በመበላት ብዛት እና በመቀደድ ከሚከሰቱት በስተቀር ለሌሎች ጥገናዎች የ3ወር ዋስትና ይሰጣል፡፡ እንደማንኛውም ዋስትና ሁሉ በአጠቃቀም እና በእርጅና ጉድለት የሚከሰቱ ብልሽቶችን ውል ሰጪ ይሸፍናል፡፡

መ/ መለስተኛ ለሆኑ የመኪና ክፍሎች እነደ እግር፤ፍሬን ሸራ፤ዲፍረንሻል፤ኤሌክትሪክ እና ፍሪሲዮን …….. ወዘተ መኪናው ከገባበት ቀን ጀምሮ ከ15 (አስራ አምስት) እስከ 20 (ሃያ) ቀናቶች ውስጥ ተሰርቶ መውጣት አለበት፡፡ ነገር ግን ከባድ ጥገና የሚያስፈልጋቸው የሞተር፤ካንቢዮ፤ሙሉ የቀለም ቅብ፤ጊር ቦክስ ስራ እና ሌሎች መኪናው ከገባበት ቀን ጀምሮ በ45 (አርባ አምስት) ቀናት ውስጥ ተጠናቀው መውጣት አለበት፡፡ ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱትን የማጠናቀቂያ ግዜዎች ከተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዳይጠናቀቅ የሚያስችል ሁኔታዎች ካጋጠሙ ለመስሪያ ቤቱ በፅሁፍ በማሳወቅ በጋራ መፍትሄ ያስቀምጣሉ፡፡

5.4 በውል ተቀባይ ማንኛውም የተሽከርካሪ የጥገና ሥራ ከተሠራለት በኋላ በጥገናው ጥራት

ችግር ምክንያት ለምሳሌ በአገጣጠም ስህተት በመለዋወጫ ዕቃ እውነተኛ /Genuine አለመሆን ወዘተ… በተሠራው ሥራ ላይ ወይም ተያያዥነት ባላቸው ክፍሎች ወይንም አካሎች ላይ ችግር ቢደርስ ለደረሰው ችግር የጥገና ወጪውን ሙሉ በሙሉ የውል ተቀባይ ይሸፍናል፡፡

5.5 ተሽከርካሪዎቹ በሚጠገኑበት ወቅት ውል ተቀባይ የሚወክለው ባለሙያ የመኪናው ሹፌርና የውል ሰጪ ተወካይ የሆኑ በጋራኛ ተገኝተው ጥገናው በትክክል መኪናውንና የተገዙት መለዋወጫዎችም መገጣጠማቸውን እንዲያረጋግጡ ውል ተቀባይ ይፈቅዳል፡፡

5.6 ውል ተቀባይ የተረከባቸውን ተሽከርካሪዎች በሥራ ትዕዛዝ ቅጽ ላይ በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተጠየቀውን አገልግሎት ሰጥቶ የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

5.7 ውል ተቀባይ በውሉ አንቀጽ 4 መሠረት የሚፈለግበትን አገልግሎት ሰጥቶ ተሽከርካሪዎቹን ለማስረከብና ክፍያውን በአንቀጽ 5 መሠረት ለመቀበል መብት ይኖረዋል፡፡

5.8 ውል ተቀባይ የውል ማስከበሪያ ከጠቅላላ ግምቱ 10% /አሥራ በሲፒኦ ያስይዛል፡፡

## አንቀጽ 6

## ስለርክክብ

6.1 ውል ተቀባይ ለጥገና በጽሁፍ ትዕዛዝ የሚላኩለትን መኪናዎች ከሹፌሩ ወይም ከተወካዩ እጅ መኪናው የሚገኝበትን ሁኔታ መርምሮና አይቶ በውስጡ ያሉ ዕቃዎችን ጭምር በዝርዝር መዝግባ በጽሁፍ ደረሰኝ ይረከባል፡፡ ውል ሰጪ የተወካዩን ስም ለውል ተቀባይ በጽሁፍ ይገልጻል፡፡

6.2 ውል ሰጪ ጥገና እና ዕደሳ የተደረገለትን መኪና በሹፌሩ ወይም ሌላ ወኪሉ አማካኝነት በትክክል የተደረገውን ጥገናና ዕደሳ አይቶና አረጋግጦ መኪናውን ለጥገና ለውል ተቀባይ በአስረከበበት ሁኔታ ፈርሞ ይረከባል

6.3 ከመኪናው የተፈቱ አሮጌ ዕቃዎችንም በሹፌሩ ወይም በሌላ ወኪል አማካኝነት ከውል ተቀባይ ፈርሞ ይቀበላል፡፡

6.4 ውል ተቀባይ ውል ሰጪ ክፍያውን በአንቀጽ ሰባት በተጠቀሰው መሰረት የማይፈጽም ከሆነ በጥገና ላይ ያሉ እና የተጠገኑ ተሽከርካሪዎችን ክፍያ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የመያዝ መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 7

## የክፍያ ሁኔታ

7.1 የሚጠየቁትን ክፍያዎች ውል ሰጪው የክፍያ ጥያቄው በቀረበለት በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ክፍሎ ወይም የዱቤ አገልግሎት መጠየቂያ ደብዳቤ በማቅረብ ይረከባል፡፡

## አንቀጽ 8

## ውሉን ለማሻሻል ወይም ስለመሰረዝ

8.1 ከሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች አንደኛው ወገን ይህ ውል እንዲሻሻል ሲፈልግ መሻሻል ይገባዋል የሚለውን ነጥብ ወይም ሀሳብ በጽሁፍ ለሌላኛው ወገን መጠየቅ ይኖርበታል የማሻሻያ ጥያቄ በጋራ ውይይት ድርድር መተማመን የሚደረስበት ከሆነ የማሻሻያ ውሉን ይፈራረማሉ፡፡

8.2 ከሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች አንደኛው ወገን ውሉን ሙሉ በሙሉ ለሚቀረጥ ቢፈልግ ከአንድ ወር በፊት ውሉን ለማቋረጥ የተገደደበትን ምክንያት እንደአመችነቱ በጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡ ውሉ ከመቋረጡ በፊት በንብረትና ገንዘብ በኩል የሚፈለግባቸውን ሁሉ በቅድሚያ መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡

8.3 ከዚህ በአንቀጽ 9.1 እና 9. 2 በተጠቀሱት መሠረት ሀሳቦች በአንደኛ ወገን ሳይታመንባቸው ቀርቶ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ የውሉን መቋረጥ የሚፈልገው ወገን በ./ሕ/ቁጥር 1823 መሠረት ውሉ እንዲፈርስ የማድረግ መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 9

## ልዩነቶችን ስለመፍታት

9.1 በሁለቱ ወገኖች መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ሁለቱም ወገኖች በጋራ ውይይት ችግሩን ለማስወገድ የየበኩላቸውን ጥረት ያደርጋሉ፡፡

9.2 ችግሩ በጋራ ውይይት መፍትሔ የማያገኝ ከሆነ በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ እና የንግድ ሕግ መሠረት ይፈጸማል።

## አንቀጽ 10

## ውሉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ውል ከዛሬ 02/11 ቀን 2018 ዓም. ጀምሮ እስከ 2018 ዓ.ም. ለአንድ ዓመት የፀና ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 11

## የውል አያያዝ

ይህ ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678፤1731/2005 መሰረት ተዋዋዮቹ መካከል ግዴታን ለማቋቋም የተደረገ ነው፡፡ ይህንን ውል ለማፍረስ የሚሞክር ወገን ቢኖር ውሉን ላከበረው ወገን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 188 እና

1890/1882 መሰረት ብር 190,767.99 (አንድ መቶ ዘጠና ሺ ሰባት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከ99/100 ሳንቲም) ተከፍሎ ውሉ በሕግ ፊት የፀና ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 12

## የውል አያያዝ

ይህ የውል በአራት ቅጂ ተዘጋጅቶ አንደኛው ቅጂ ውል ሰጪ መዝገብ ቤት ሁለተኛው ቅጂ ሶስተኛው ቅጅ ለግዥ ክፍል አራተኛው ቅጅ በውል ተቀባይ እጅ ይቀመጣል፡፡

**ስለ ውል ተቀባይ**

ስም Mr. Solomon Tafesse Lulu, Deputy CEO Manufacturing

ፊርማ ------------------------------

ቀን ------------------------------

**ስለ ውል ሰጪ**

ስም ------------------------------

ፊርማ ------------------------------

ቀን 06/11/2018

The Federal Democratic Republic of Ethiopia, Ethiopian Biodiversity Institute

**ምስክሮች /እማኞች/**

1. ስም ---------------- ፊርማ ---------------- ቀን 01/11/18
2. ስም ---------------- ፊርማ ---------------- ቀን ----------------

FDRE Technical and Vocational Institute Technobizin Enterprise